ጥር 16/2004 ዓ.ም

# የመኢአድ 38 አባላት በደቡብ ኢትዮጵያ ታሠሩ።

## *ሃያ አንዱ ኢህአድግን ትተው ወደ መኢአድ የመጡ ናቸው።*

በደቡብ ኢትዮጵያ በጎፋ ልዩ ዞን በሦስት ወረዳዎች ውስጥ በስድስት የተለያዩ አካባቢዎች ከጥር 8/2004 ዓ.ም ጀምሮ 38 የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) አመራርና አባላት በገዥው ፓርቲ የታሠሩ መሆናቸውን አቶ እንድርያስ ኤሮ የመኢአድ ማዕከላዊ ሥራ አስፈፃሚኮሚቴ አባልና የደቡብ ቀጠና ኃላፊ ለመኢአድ ህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ገለፁ።

እንደ አቶ እንድርያስ ኤሮ ገለፃ በሰላማዊ መንገድ በነፃ የመደራጀትና የመታገል መብትን በተፃረረ ሁኔታ የገዥው ፓርቲ በመኢአድ አባላት እየወሰደ ያለው የማሰር እርምጃ እየቀጠለ መሆኑን ጠቅሰው ዝርዝሩንም እንደሚከተለው አብራርተዋል።

በጎፋ ልዩ ዞን በዛላ ወረዳ አምቤ ኃይሌ ቀበሌ የመኢአድ የቀበሌውን ሰብሳቢ አቶ እጅጉን ተክሌን ጨምሮ አስር (10) የመኢአድ አባላት ከጥር 9/2004 ዓ.ም. ጀምሮ በኢህአዴግ የታሠሩ መሆናቸውን ገልጸዋል። ሁኔታውን ሲያስረዱም አቶ እጅጉ ተክሌ በጎፋ ልዩ ዞን ከተማ ሳውላ ደርሰው የዘጠኙን አባላት ስም ዝርዝር ይዘው ወደ አካባቢያቸው ሲመለሱ ፖሊሶች እሳቸውንና በያዙት ዝርዝር መሠረት ሌሎቹንም ከሚኖሩበት አካባቢ 35 ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ በመውሰድ እንዳሠሯቸው ጠቅሰዋል።

በተመሳሳይም በዚሁ በዛላ ወረዳ በሳልቤ ቀበሌ የመኢአድ የኡባ ጎፋ ወረዳ ሥራ አስፈፃሚ አባላት የሆኑት አቶ ወደራ ወንታ እና አቶ አሽትሬ ጢቆ የመኢአድ ቲ ሸርት ለብሰው የአቶ ወደራ ወንታን ልጅ ለመጠየቅ ወደ ዛላ ድንበር ሲሄዱ በዛላ ወረዳ የኢህአዴግ ሥራ አስኪያጅ፣ በአንድ የካቢኔ አባልና በፖሊስ ከጥር 9/2004 ዓ.ም ጀምሮ ታስረዋል። የታሰሩትም ከሚኖሩበት አካባቢ 80 ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ዛላ ፖሊስ ጣቢያ መሆኑን አቶ እንድርያስ አስታውቀዋል።

የመኢአድ የደቡብ ቀጠና ኃላፊ ማብራሪያቸውን ሲቀጥሉም የዛላ ወረዳ የሴሎ ቦሎ ቀበሌ የመኢአድ ሰብሳቢ አቶ ዮሴፍ ያቻ አንድ ሄክታር መሬታቸውን በገዥው ፓርቲ ካድሬዎች በመቀማታቸው ለዛላ ወረዳ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረባቸውንና ፍርድ ቤቱ ይመለስላቸው ብሎ ቢፈርድላቸውም ቀበሌው ለመመለስ ፈቃደኛ በለመሆኑ ለወረዳ አስተዳዳሪው አቤት ሲሉ ከጥር 10፣2004 ዓ.ም. ጀምሮ በፖሊስ እንዲታሠሩ ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

የማዕከላዊ ኮሚቴሥራ አስፈፃሚ አባልና የደቡብ ቀጠና ኃላፊው ስለደምባ ጎፋ የመኢአድ ታሳሪዎችም የሚከተለውን ብለዋል። ቀደም ሲል ታህሳስ 16/2004 ዓ.ም. በ«ዘንጋ አዋንዴ» ቀበሌ

ውስጥ ታስረው ከነበሩት ሃያ ሰባት (27) የመኢአድ አመራርና ሌሎች አባላት ውስጥ አሁን በድጋሚ ስድስቱን የገኘው ፓርቲ ካድሬዎች ማሰራቸውን ጠቅሰው አምስቱ ጥር 10 እና አንደኛው ግን ጥር 15/2004 ዓ.ም መታሰራቸውን አስረድተዋል፡፡ ባሎቻቸው ለጊዜው ባለመገኘታቸው ምክንያት ሁለት ሚስቶችም አብረው ታስረው እንደነበረና አንደኛዋ ሴት በዕድሜ የገፋ በመሆናቸው እስር ቤት እንዳያድሩ ሲደረግ ሌላዋ ሴት ግን ባለቤታቸው እስከሚገኙ ድረስ በልዋጭ ታስረው ማደራቸውንም ጠቁመዋል፡፡ የመታሠራቸውን ምክንያት ሲገልጹም ብር 1,300.00 እየከፈሉ አለፍላጎታቸው የግድ ማዳበሪያ እንዲወስዱ መታዘዛቸውንና እነሱም የገዥው ፓርቲ ለራሱ አባላት ለማዳበሪያ መግዣ ብድር እንደሚሰጥ፣ በሴፍቲ ኔት በማቀፍ የጉልበት ሥራ ሠርተው ገንዘብ እንዲያገኙ ሁኔታዎች እንደሚመቻችላቸው እና ይህ ሁኔታ ግን ለመኢአድ አባላት የማይፈቀድ በመሆኑ በሌለ አቅማችን ለመግዛት አንገደድም በማለታቸውና የግለ ሰብ ማሳም አለባለቤቱ ፈቃድ አንቆፍርም በማለታቸው መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ለመፈታት የሚችሉት በእስር ቤት ውስጥ ይጠብቋቸው ለነበሩ ጠባቂዎች እያንዳንዳቸው ብር 25.00 ሲከፍሉ መሆኑንም እንደተነገራቸውም አቶ እንድርያስ ገልጸዋል፡፡

ደምባ ጎፋ ወረዳ በኦባ ባንዳ ወረዳ የመኢአድ አባል የሆነት አቶ የዳ መቶ ከጥር 8 እስከ ጥር 11/2004 ዓ.ም. ድረስ በገዥው ፓርቲ አባላት መታሠራቸውን አቶ እንድርያስ ኤሮ ጨምረው ጠቅሰዋል፡፡ አቶ ጴጥሮስ ፌቀ የጢቀ ቀበሌ የመኢአድ አመራር አባል አቶ የዳ መቶን ለማስፈታት ከሳውላ የመኢአድ የዞን ጽ/ቤት ደብዳቤ አጽፈው እስር ቤት በሄዱበት ወቅት አንተንም እንፈልግሃለን ተብለው ከጥር 8/2004 ዓ.ም. ጀምሮ በእስር ላይ እንደሚገኙ የደቡብ ቀጠና ኃላፊው አስታወቀዋል፡፡

በመጨረሻም በኡባ ወረዳ ያምባላ ቀበሌ የኢህአዴግ አባላት የነበሩ ሃያ አንድ (21) ሰዎች ጥር 6/2004 ዓ.ም. የኢህዴግ አባል ሆነው መቀጠል የማይፈልጉ መሆናቸውንና ከፓርቲው መልቀቃቸውን ገልጸው ደብዳቤ ካስገቡ በኋላ ጥር 7 2004 ዓ.ም. የመኢአድ አባል ለመሆን ማመልከቻ ለመኢአድ ማቅረባቸውን ተከትሎ የገዥው ፓርቲ የመኢአድ አባል መሆን አትችሉም ብሎ ሃያ አንዱንም ጥር 8/2004 ዓ.ም. ጀምሮ ያሠራቸው መሆኑን አቶ እንድርያስ ኤሮ ለህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ጠቅሰዋል፡፡

በደቡብ ኢትዮጵያ በጎፋ ልዩ ዞን የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የዞኑን ጠቅላላ ጉባዔ ጥር 5/2004 ዓ.ም በሳውላ ከተማ በደማቅና በተሳካ ሁኔታ ማካሄዱ ይታወሳል፡፡